# ብ ር ሀ ና ማ ብ ዕ ር

*ከሥርጉተ ሥላሴ*
*ሕዳር 2001 ዓ. ም.*



## Astrid Lindgren

ዓለም አቀፏ፣ ልዩዋና ድንቋ አስትሪድ ሊንድግረን / Astrid Lindgren / እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ሕዳር 14 / 1907 በሀገረ ስዊዲን ሰሜላንድ ልዩ ሥፍራው ኔስ በሚባል ከተማ ተወለዱ:: እንደ እኔ ይህ ቀን ዓለም አቀፍ የብዕር ዳግም ትንሣኤ ነው ማለትም ይቻላል:: ዓለም አቀፏ ኮበብ ደራሲ የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አሁንም እንደ ሥርጉተ ሥላሴ እይታ ሼክ ስፒርም፣ አሪስቶትልም እንደገና ተወለዱ የሚል ዕድምታ ላይ ደርሻለሁ:: በእውነቱ ደራሲዋ የዓለም የልጆች፣ የመብት አስከባሪ፣ ጠበቃ ፣ ሚኒስትር እና አምባሳደር ናቸው:: የአስትሪድ ሊንግሪድ የሥነ ጥብብ ሥራዎች ባህላዊ ወይንም ክላሲካል ሆነው ፍጹም የልብ ማህተም የሆነውን የልጅነት ሕይወት ክፍለ ጊዜ መነሻ አድርጎ በፈጠራ የጥበብ ቅመም የተከሸነ ወግን፣ ልማድን፣ትውፊትን፣የቤተሰብ ፍቅር ማህበራዊ ኑሮን በሚገባ ያገናዘበ ሲሆን ብዙ ሥራዎቻቸው ከሀገራችን ከኢትዮጵያ ሕይወት ጋር ቅርበት ያለው ሆኖ አግኝቸዋለሁ:: የጥበብ ሥራወቻቸው ምንጭ እና አትኩሮት ስለ ቤተሰብ አልባ ልጆች፣ ተስፋ ስላጡ ልጆች፣ ስለተሰደዱ ልጆች በልጅነታቸው ስለሚሞቱ ልጆች፣ ስለ ድሀ ልጆች ዕጣ ፋንታ እጅግ በጥልቅ የጥናት ሥራ የተሠራበት ነው::

ልብ ወለድ ብቻ አይደለም:: ፍልስፍናም አለበት :: ለዚህም ነው ለእኔ ልዩ ጣዕምና ለዛ የሰጠኝ። ደራሲዋ የሴቶች ዘውድ፣ የተግባር ጀግና ፣ የድርጊትም ልዕልት ናቸው:: ባለፈው ዓመት እ.ኤ.አ ህዳር 14 / 2007 መቶኛ ዓመታቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲከበር ከወጡት የተለያዩ ማስረጃዎች እንዳገኙት ጠቅላላ የፃፉት መጽሐፍት ብዛት 70 ሲሆን በ 90 ቋንቋዎች ተተርጉሞ በ 130 ሚሊዮን ቅጅ ተባዝቶ ለታዳሚዎች ተደርሷል። ይህ የብዕር ፏፏቴ ምንጩ ከየት ይሆን? ደራሲዋ መንፈስ - ይሆኑ? ... ? .....? ወይንስ የሰው ልጅ፤ ወይንስ አንድ ፍጡር ለእኔ ህሊና መልስ የለውም::

ዓለም አቀፏ ደራሲ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ የሥነ ጽሑፍ ድርጅቶች፣ በጀርመን ሀገርም እንዲሁ በተወለዱበት ሀገርም የበርካታ ሽልማቶች ባለበት ለመሆን ’ ችለዋል:: ወሸኔ ነው - ማለፊያ - ! የአንስት ጌጥ ! ልዩ - ፈርጥ ! በሌላ በኩል ደግሞ ብቸኛው ደራሲ የፊልም ዳይሬክተርም ናቸው! ድንቅ ! የመጀመሪያ ሥራዎች ፒፒ ሎንግ ሽቶኪንግ / Pippi Long stocking / ሲሆን በ72 ሀገር ቋንቋዎች ተተርጉሟል:: ኢትዮጵያ ግን ከዝርዝር የለቸም:: ምን ይሰማችኋል ውድ የብዕር ገበሬዎች ? ሌላው ዓለም አቀፏ ወደርም አቻም የሌላቸው የልጆች መጽሐፍት ፀሐፊዋ መዝሙርም አላቸው:: መዝሙሩ እራሱ ልዩ ቃና አለው። ስታዳምጡትም የባዕድ ሀገር ሆኖ አይሰማችሁም:: በጠቅላላ ሥራዎቻቸውን መሠረት ያደረገ እስከ አለፈው ዓመት መጨረሻ ድረስ 120 የጥናት ፣ የምርምር ፣ የሕይወት ታሪክ፣ የፊልም፣ የቲያትር እና የመዝሙር የጥበብ አዝመራ በጣም በስፋት ተዘምሮበታል:: ይህ የእሳቸው የመንፈስና የህሊና ምርት አሁንም ህትመቱ ቀጥሏል :: በተረፈ እኔ በግሌ ለመታሰቢያነት ከሠራሁት ግጥም ውስጥ ጥቂቱን ስንኝ በ “ ZAU “ መጽሔት ላይ የወጣውን ብቻ “ የብርሀን ብዕር “ የሚለውን እስቲ ለቅምሻ ትላለች የእኔ ክቡሯ ብዕሬ ::

አንድ ነገር ልበልና ነገሬን ልከውን:: ትውልዳዊ ድርሻውን ከበቂ በላይ የተወጡትን ዓለም አቀፏን ደራሲ አስትሪድ ሊንድግረንን በጣም እጅግ በጣም እንደምወዳቸው - እንደማከብራቸው መግለጥ ያለብኝ ይመስለኛል::

**መልካም የንባብ ጊዜ ! ! !**

# Der Lichtstift

*sergute selassie*



Stern – Autorin
schönste Künstlerin
die Frauen Krone.

Nummer eins in der Epoche Bleistift
perfekt.

natürlich, viel getan
überdacht

Astrid – mütterlich
echt gut.

linear
bekannt.
Astrid Lindgren

hat eine vollkommene Erinnerung

vorbildliche Freude
Wachskerzen.

Goldener Kopf
Kapazität ist hoch

ohne Zeit verloren
zufrieden.

Sanfter Betrieb
kinderlieb

der Lichtstift
Liebe gewinnen sein.